www.chilot.me

አንደኛ ዓመት ቁጥር 3
1st Year No 3

ሐረር መጋቢት 5 ቀን 1988
Harar, March 14 1996

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
HARAR NEGARI GAZETA
HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 3/ 1988

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ

አዋጅ ቁጥር 3/ 1988 .............................................. ገጽ 17

**የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥትና በሌሎች ሕጎች የተረጋገጡት መብቶችና ነፃነቶች በክልላችን ውስጥ መከበር ለክልላችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ዋነኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብ፣

ፍትህ የሰፈነበት ሥርዓት ለመገንባት የክልሉ የዳኝነት ሥራ አካሄድና አደረጃጀት በአዲስ መልክ መዋቀሩ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነፃ ፍርድ ቤቶችን ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

እንዲሁም የክልሉ ፍርድ ቤቶችና ዳኞች ተግባራቸውን በነፃ እንዲያከናውኑ የሕግ ዋስትና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን በማመን እና የክልሉ ዳኞች አሿሿም፣ ስንብት፣ እድገትና የሥነ-ምግባር ሁኔታዎችን በሚመለከት በዳኝነት ሥራ ከማናቸውም ተፅዕኖ ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲያስችል ገለልተኛና ነፃ የሆነ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ስለመገንዘብ፣

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ26/2/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፦

www.chilot.me



ሀ. "የክልሉ መንግሥት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47/1/9 መሠረት የተቋቋመ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው።"

ለ. "የክልሉ ሕገ-መንግሥት" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ነው።

ሐ. "የክልሉ ምክር ቤት" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው።

መ. "የፌዴራል ሕገ-መንግሥት"ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው።

ሠ. "ክልሎች" ማለት በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47/1 የተዘረዘሩት የፌዴራሉ ክልሎች አባላት ናቸው።

ረ. "የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፍርድ ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 እና 25 መሠረት የተቋቋሙት የክልሉ መደበኛ እና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ናቸው።

ሰ."የሸሪዓ ፍርድ ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 25 መሠረት የተቋቋሙ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ናቸው።

ሸ."መደበኛ ፍርድ ቤቶች" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ናቸው።

ቀ. "ዳኛ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የዳኝነት ሥራ እንዲያከናውን በክልሉ ምክር ቤት የተሾመ ነው።

በ."የክልል መንግሥት ሠራተኞች" ማለት በክልሉ መንግሥት በተቋቋሙ ልዩ ልዩ ቢሮዎችና የክልሉ መንግሥት ተቋሟት ሥር ተቀጥረው የሚያገለግሉ ሠራተኞች ናቸው።

ተ. "ሰው" ማለት በተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው።

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ስለ ክልሉ ፍርድ ቤቶች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ስለ ሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መደበኛ ፍርድ•ቤቶች መቋቋምና ስለ ዳኝነት ሥልጣናቸው</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

3. <u>መደበኛ ፍርድ ቤቶችን ስለ ማቋቋም</u>

በዚህ በታች የተመለከቱት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመዋል።

1. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ከዚህ በኋላ "ጠቅላይ ፍርድ ቤት" እየተባለ የሚጠራ፣

2. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ከዚህ በኋላ "ከፍተኛ ፍርድ ቤት" እየተባለ የሚጠራ እና

3. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ከዚህ በኋላ "የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት" እየተባለ የሚጠራ።

4 <u>ዓላማዎች</u>

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች፡-

1. በፌዴራሉና በክልሉ ሕገ-መንግሥት የተረጋገጡትን ልዩልዩ መብቶች፣ ነፃነቶችና ጥቅሞችን የማስከበር፣

2. ፍትህና ሠላም እንዲሰፍንና ሕግና ሥርዓት እንዲጠበቅ የማድረግ እና

3. ሕብረተሰቡ ለሕግ ተገዢ እንዲሆን የማስተማር ዓላማዎች አሏቸው።

5. <u>የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፍርድ ቤቶች አጠቃላይ የዳኝነት ሥልጣን</u>

1. የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶችና በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 17/2 እንደተመለከተው በሌላ ሕግ የዳኝነት ሥራ እንዲያከናውኑ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በሐረሪ ሕዝብ ክልል የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፍርድ ቤቶች በየደረጃቸው በሕግ የተወሰኑላቸውንና ተፈፃሚ ነት ባላቸው ባልተሻሩ ነባር ሕጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች አይተው የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል።

www.chilot.me



ንዑስ ክፍል ሁለት
የሐረሪ ሕዝብ ክልል መደበኛ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አጠቃላይ የዳኝነት ሥራ አካሄድ

6. የክልሉ መደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና ሠራተኞች

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዚዳንትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል።
2. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል።
3. የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል።
4. ማንኛውም የክልሉ ፍርድ ቤት ለሥራው የሚያስፈልጉ ሬጂስትራሮችና ሠራተኞች ይኖሩታል።

7. የችሎቶች አሠራር

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች ይኖራቸዋል።
2. በጠቅላይ ፍርድ ቤትና በከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንድ ችሎት አንድ ሰብሳቢ ዳኛና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ።
3. የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በሌለበት ወይም ከችሎት የማይገኝበት ሁኔታ ካጋጠመ ከሰብሳቢው ቀጥሎ ያለው ዳኛ ሰብሳቢ ይሆናል።
4. የየፍርድ ቤቶቹ ፕሬዚዳንቶች በየፍርድ ቤቶቻቸው በማንኛውም ጊዜ ሰብሳቢ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ።
5. ማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት በአንድ ዳኛ ይመራል።
6 በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች በክልሉ ውስጥ ምቹ በሆኑ ሥፍራዎች ያስችላሉ።

8. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች ግልጽ በሆነ ቦታና ሁኔታ ያስችላሉ። ሆኖም ለዳኝነት አሠራር አግባብ ባላቸው ሕጎች የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው፡-
ሀ. ለሕዝብ ሠላምና ፀጥታ አስፈላጊ ሲሆን ወይም
ለ. የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት ሊያስችሉ ይችላሉ።

9. የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

1. የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ ሐረሪና ኦሮምኛ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ በተመለከቱት ቋንቋዎች መጠቀሙ እንዲጀመር በክልሉ ምክር ቤት እስኪወሰን በአማረኛ ቋንቋ መጠቀሙ ይቀጥላል።
3. የክልሉን ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ ለማያውቁ ተከራካሪዎች መንግሥት አስተርጓሚ ይመደብላቸዋል።

10. ከችሎት ስለመነሳት

በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኛ አንድን ጉዳይ በሕግ እንዳያይ ከተከለከለ ከችሎት የሚነሳበት ሁኔታ በሕግ በተወሰነው መሠረት ይሆናል።

11. ጠበቃ የማቆም መብት

1. ማንኛውም ሰው በመረጠው የሕግ ጠበቃ የመወከል መብት አለው።
2. ጠበቃ ለማቆም አቅም ለሌለውና በወንጀል ለተከሰሰ ሰው ያለ ጠበቃ መከራከር ፍትህ ሊጓደልበት ይችላል ብሎ ችሎቱ ሲገምት መንግሥት ጠበቃ ይመድብለታል።

12. የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉን ፍርድ ቤቶች በሙሉ ይወክላል።
2. የክልሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ የሆኑትን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል።
3. የክልሉን ፍርድ ቤቶች የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
4. የመደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን ይደለድላል።
5. ወንጀልን ለመከላከልና የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ከክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት፣ ከፍትህና ፀጥታ ዘርፍ እና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል።

www.chilot.me



6. ስለ ክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ ለክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንትና ለምክር ቤቱ ጥናታዊ ዘገባ ያቀርባል።
7. የውልና ማስረጃ ምዝገባ ሥራን ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
8. የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉባዔ አጀንዳን ያዘጋጃል፣ ስብሰባውንም ይጠራል።
9 የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉባዔ ላይ መገኘት የሚገባቸውን ተሳታፊዎች ብዛት ይወስናል።
10. የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉባዔ ለክልሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያቀርባቸውን የሕግ ረቂቆች ያዘጋጃል።
11. ስለክልሉ ፍርድ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ በእስታትስቲክ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል።
12. የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሕግ መጽሔት እንዲዘጋጅ ያደርጋል።
13. ትምህርታዊ የሆኑ የየዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው እንዲታተሙ ያደርጋል።
14. የክልሉን ፍርድ ቤቶች ያደራጃል።
15. በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

13. <u>የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት

1. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፣
3. ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክትል ፕሬዘዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱ ከዳኞች አንዱን ተክቶት እንዲሠራ ሊወክል ይችላል።
4. ፕሬዚዳንቱ በማይሰየምበት በየትኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች ሰብሳቢ ሆኖ ሊሠራ ይችላል።

14 <u>የክልሉ መደበኛ ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ፍርድ ቤቶቻቸውን ይወክላሉ፣
2. በየፍርድ ቤቶቻቸው የተመደቡላቸውን ሠራተኞች ይቆጣጠራሉ፣
3. በየፍርድ ቤቶቻቸው የተመደቡላቸውን ዳኞች ይደለድላሉ፣ አስተዳደራዊ የሆኑ ጉዳዮች በበላይነት ይመራሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣
4. የየፍርድ ቤቶቻቸውን የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅተው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባሉ፣
5. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አማካይነት ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ የፀደቀላቸውን የሥራእቅድ ሥራ ላይ ያውላሉ፣
6. ስለሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው በእስታቲስቲክስ የተደገፈ መግለጫ በየጊዜው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀርባሉ፣
7. ትምህርታዊ የሆኑ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲላኩ ያደርጋሉ፣
8. በማይኖሩበት ጊዜ በፍርድ ቤቶቻቸው ካሉ ዳኞች አንዱን ተክቶአቸው እንዲሠራ ሊወክሉ ይችላሉ፣
9. ሌሎች በሕግ የሚሠጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ።

<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

<u>የክልሉ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን</u>

15. <u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. ከክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ተቀብሎ ይዳኛል፣
2. በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78/2 በተደነገገው መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይኖረዋል፣
3. መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

16. <u>የክልሉ መደበኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ሥር ባሉ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት፣ በፍትሃ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ እና በሌሎች ሕጎች በመጀመሪያ ደረጃ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታዩ የተደነገጉትን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፣
2. በተጨማሪም በክልሉ መደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጡ ፍርዶች

www.chilot.me



/ውሳኔዎች/፣ ብይኖች ወይም ትዕዛዞች ላይ በሕጉ መሠረት የሚቀርቡለትን ይግባኞች ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፣
3.እንዲሁም በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ78/2 ሥር እንደተደነገገው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይኖረዋል።

17. የክልሉ መደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን

1. የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በክልሉ ሥልጣን ሥር ባሉ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት፣ የፍትሃ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በሌሎች ሕጎችና ደንቦች ቀድሞ በአውራጃና በወረዳ ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ የተደነገጉትን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል።
2.እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የዳኝነት ነክ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት በሚሰጡት ውሣኔዎች፣ ብይኖች ወይም ትዕዛዞች ላይ በሕጉ መሠረት የሚቀርቡለትን ይግባኞች ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል።

18. የክልሉ መደበኛ ፍርድ ቤቶች አጠቃላይ የክልል /የግዛት/ ሥልጣን

የክልሉ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የክልል ውይም የግዛት ሥልጣን መላውን የሐረሪ ሕዝብ ክልል ያጠቃልላል።

ክፍል ሁለት
የዳኝነት ነፃነት

19. ዳኞች በዳኝነት ሥራቸው ነፃ ስለመሆናቸው

1. የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኞች የዳኝነት ሥራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፣ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፣
2. ዳኞች ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅእኖ ነፃ ናቸው፣
3. ማንኛውም የክልሉ ዳኛ ከዚህ በታች በተደነገጉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር እድሜው60 (ስልሣ) ዓመት ከመድረሱበፊት ያለፈቃዱ ከዳኝነት ሥራው ሊነሳ አይችልም፣
ሀ.የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና እንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም
ለ. በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢ ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን፣ እና
ሐ. የጉባዔው ውሳኔ በክልሉ ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምጽ ሲጸድቅ፣
4. ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳኛ ሥራውን በፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግ ከመልቀቁ በፊት 2(ሁለት) ወር አስቀድሞ በጽሁፍ ለሚመለከተው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማሳወቅ አለበት።

20. ዳኛ ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ለፌዴራሉና ለክልሉ ሕገ መንግሥቶች ተገዥ የሆነ፣
2. በሕግ ትምህርት የሰለጠነ ወይም በልምድ ሰፊ የሕግ እውቀት ያለው፣
3. በሥነ-ምግባርና በታማኝነት መልካም ስምና ዝና ያለው፣
4. ዕድሜው ከ 25 /ሃያ አምስት/ ያላነሰ፣
5. ቢቻል የክልሉ ተወላጅ የሆነ፣
6. የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ፣
7.ፖለቲካ ነክ ባልሆነ ወንጀል ተከሶ በእስራት ያልተቀጣ፣
8. በዳኝነት ሙያ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ፤

21. የዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የየፍርድ ቤቶቹ ዳኞች በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ39 በተመለከተው መሠረት ይሾማሉ።

22. ቃለ መሐላ

በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የተሾሙ ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ለክልሉ ሕዝብ ያላቸውን ታማኝነት የሚገልጽ ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ።

23. የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ከሥራቸው እንዲነሱ ስለሚደረግበት ሁኔታ

የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትን በተመለከተ በአንቀጽ 19/3/ሀ እና ለ-

www.chilot.me



የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ጉዳዩ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ፕሬዚዳንት በሚቋቋም ልዩ ኮሚቴ ታይቶ የውሣኔ ሐሳቡ በምክር ቤቱ ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ከሥራቸው ሊነሱ ይችላሉ።

24. ከዳኝነት ሥራ ጋር አጣምሮ ለመሥራት ስለተከለከሉ ሁኔታዎች

1. ማንም የክልሉ ዳኛ በዳኝነት ሥራው ላይ እያለ የሕግ አውጪ አካል፣ የሕግ አስፈፃሚ አካል፣ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሊሆን አይችልም፣

2.በንዑስ አንቀጽ1 የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም የክልሉ የጎኛች አስተዳደር ጉባዔ ወዲያውኑ ጉዳዩን ለክልሉ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ እንዲሁም የክልሉ ምክር ቤት ወይም የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ዳኛው በየትኛውም ችሎት እንዳይሰየም ያደርጋል።

## ክፍል ሦስት
## የሸሪዓ ፍርድ ቤት

25. በዚህ አዋጅ በምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 3 ከተቋቋሙት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሌላ የሚከተሉት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመዋል።

1. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣
ከዚህ በኃላ
"ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት" እየተባለ የሚጠራ፤እና

2. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣
ከዚህ በኃላ፣
"የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት" እየተባለ የሚጠራ፤

26. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አጠቃላይ የዳኝነት ሥልጣን

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 እና 30 የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በክልሉ ሙስሊም ሕብረተሰብ አባላት መካከል፣ ወይም በክልሉ ሙስሊም ህብረተሰብ ሥር በሚተዳደሩ ኃይማኖታዊ ተቋማት መካከል ወይም በክልሉ ሙስሊም ሕብረተሰብ አባልና /አባላትና/ በተቋሙ /በተቋማቱ/ መካከል በሚነሱ፦

ሀ. የወቅፍ ጉዳዮች፣
ለ. የውርስ፣የኑዛዜ እና የስጦታ ጉዳዮች፣
ሐ. የተቋማቱየአስተዳደር ጥያቄዎች እና
መ. የጋብቻና የፍቺ እንዲሁም ከዚህ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፣

2. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት "ወቅፍ" ማለት መስጊዶችን ጨምሮ ለእስላምና ኃይማኖታዊ ተቋማት በስጦታ የሚሰረከቱ ማናቸውም ዓይነት ንብረቶች ማለት ነው።

27. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የክልል /የግዛት/ ሥልጣን

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የክልል ወይም የግዛት ሥልጣን መላውን የሐረሪ ሕዝብ ክልል ያጠቃልላል።

28. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ

የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን የሚያከናወኑት በሸሪዓ ሕግና በሐገሪቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው።

29. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት [illegible] የሰጠው ውሣኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ [illegible] የሚቀርቡለትን ይግባኞች ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል።

2.በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 15/3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፣

3. የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓትና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሥልጣን በኢትዮጵያ የፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት የሚወሰኑ ይሆናሉ፣

30. የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 26 የተመለከቱትን ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል።

31. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት

www.chilot.me



1. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት እና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል፤
2. የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኞችና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ሊኖሩት ይችላል፤
3. የትኛውም የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሬጅስትራሮች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፤

32. <u>የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ችሎቶች</u>

1. የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እያንዳንዳቸው ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች ይኖራቸዋል፤
2. በእነዚህ ፍርድ ቤቶች በእያንዳንዱ ችሎት አንድ ሰብሳቢ እና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ፤
3. የችሎት ሰብሳቢ በሌለበት ወይም ከችሎት የሚነሳበት ሁኔታ ካጋጠመ ከሰብሳቢው ቀጥሎ ያለው ዳኛ ሰብሳቢ ይሆናል፤
4. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎቶች በማንኛውም ጊዜ ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፤
5. በተጨማሪም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7/6 እስከ አንቀጽ 11/1 የተደነገጉት ለሸሪዓ ፍር ድ ቤቶችም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

33. <u>የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 14 ለክልሉ መደበኛ ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

34. <u>የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች አሿሿምና የዲሲፕሊን ሁኔታ</u>

በዚህ ክፍል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በአንቀጽ 19፣ 20፣ 21፣ 22 እና 23 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሸሪዓ ፍርድቤቶችም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

35. <u>ዳኛ ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 20 የተመለከቱት በንዑስ አንቀጽ2 የተመለከተውን ሳይጨምር ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶችም ተፈፃሚ መሆናቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ለመሆን፤

ሀ የአረበኛ ቋንቋ ችሎታ ያለው፣

ለ. ።ሸሪዓ ሕግ የሠለጠነ ወይም የሥራ ልምድ ያለው ወይም በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የበላይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚቋቋም ጊዜያዊ አጣሪ ኮሚቴ የሸሪዓ ሕግ እውቀት ያለው ለመሆኑ የተረጋገጠ እና

ሐ. በሥልጠናም ሆነ በልምድ የተገኘ ቢሆንም ከሐገሪቱ ሕጎች ቢያንስ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ እውቀት ያለው መሆን አለበት።

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## የክልሉ <u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ</u>

36. <u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ስለማቋቋምና ስለ አባላቱ</u>

1. የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኃላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. ጉባዔው ቀጥሎ የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ. የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት...... ሰብሳቢ

ለ. የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት........................ አባል

ሐ. አንድ የሕዝብ ተውካዮች ጉባዔ ተወካይ.................... አባል

መ. አንድ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ ተወካይ..................... አባል

ሠ. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት................ አባል

ረ. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት.................... አባል

ሰ. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት............... አባል

3. ጉባዔው ከማንኛውም አይነት ተፅዕኖ ነፃ የሆነና ራሱን የቻለ የአስተዳደር አካል ነው፤

4. ጉባዔው የራሱ የሆነ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል።

37. <u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ቀጥሎ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

www.chilot.me



1. የዳኞች ምልመላ፣ ምደባ፣ እድገትና ዝውውር እንዲሁም የዲሲፕሊን ሁኔታን በተመለከተ፦

ሀ. በዚህ አዋጅ ስለ ክልሉ ዳኞች አሿሿም በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት በአንቀጽ 20 እና 35 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ግለሰቦችን አጣርቶና መልምሎ በእጩነት የማቅረብ፣

ለ.ከበታች ፍርድ ቤት ወደ በላይ ፍርድ ቤት በእድገት የሚዛወሩ ዳኞችን መምረጥና ለሹመት የማቅረብ፣

ሐ. የተሾሙ ዳኞችን ምደባ የመወሰን፣ እና

መ.የዳኞች የዲሲፕሊን ደንብ የማውጣትና በደንቡ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ዳኛ የዲስፕሊን እርምጃ የመውሰድ ወይም ከሥራ እንዲወገድ ሲወሰን የውሣኔ ሐሳቡን ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ሥልጣን ይኖረዋል፤

2.በሚያወጣው ደንብ መሠረት ሬጅስትራሮችን የመምረጥ፣ የመሾም፣ የአገልግሎት ዘመንና ስንብትን፣ እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ና ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይወስናል፤

3.እንዲሁም ከዚህ በሚይ ከተሰጡት ሥልጣን ና ተግባራት በከፊል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

38. <u>የጉባዔው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1.ከጉባዔው አባላት አምስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

2.ማንኛውም የጉባዔው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤

3.ድምጽ እኩል ሲከፈል ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

4.ከዚህ በታች በአንቀጽ 39(3) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው መደበኛ የስብሰባ ቀናት ለመወሰን ይችላል። እንዲሁም ከጉባዔው አባላት አምስቱ አስቸኳ ይስብሰባ እንዲጠራ ለሰብሳቢው በጽሑፍ ሲገልጹ ሰብሳቢው ስብሰባውን የመጥራት ግዴታ አለበት።

39. <u>የሰብሳቢው ሥልጣንና ተግባር</u>

የጉባዔው ሰብሳቢ፦

1.የጉባዔው ጽህፈት ቤት በሚገባ መደራጀቱን ያረጋግጣል፤

2. የጉባዔውን ጽ/ቤት በበላይነት ይመራል፤

3. የጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውንም በሊቀ-መንበርነት ይመራል፤

4. ለዳኝነት እና ለሬጂስትራርነት ብቃት አላቸው የሚላቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር ለጉባዔው ያቀርባል፣ ስለ ህይወት ታሪካቸውም አጭር መግለጫም ይሰጣል፤

5. ጉባዔው በእጩ ዳኝነት የተቀበላቸውን እንዲሾሙ ስም ዝርዝራቸውን ከአጭር የህይወት ታሪካቸው መግለጫ እና ከጉባዔው አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል። ሆኖም የክልሉ መደበኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት እጩ ዳኞች እንዲሾሙ ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት ስለ እጩ ዳኞቹ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ የክልሉ ጉባዔ በሚያዘው መሠረት የእጩ ዳኞቹን ስም ዝርዝር ለፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የመላክ ኃላፊነት አለበት፤

6. የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በተላከለት መሠረት ስለ እጩ ዳኞቹ የሰጠውን አስተያየት ለክልሉ ጉባዔ ያቀርባል።ጉባዔውየቀረበለትን አስተያየት መርምሮ እጩ ዳኞቹ እንዲሾሙ ቀድሞ በወሰነው አቋሙ ከፀና የስም ዝርዝራቸውን ከሕይወት ታሪካቸው መግለጫ፣ ከፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እና ከክልሉ ጉባዔ አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤

7.በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 81/4 እንደተደነገገው የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ስለ እጩ ዳኞቹ ያለውን አስተያየት በ3 (ሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ጉባዔ ያልላከ እንደሆነ ጉባዔው በሚያዘው መሠረት የእጩ ዳኞቹን ስም ዝርዝር ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤

40 <u>የጉባዔው ውሳኔ አፈፃፀም</u>

ማንኛውም የጉባዔው ውሳኔ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 37/1 /-መ- እንደተደነገገው ከሥራ ማስወገድን የሚመለከት የዲሲፕሊን እርምጃ ካልሆነ በስተቀር የመጨረሻና የፀና ይሆናል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ስለ ክልል ፍርድ ቤት ጉባዔ</u>

41. <u>የክልል ፍርድ ቤት ጉባዔ</u>

1. የክልሉ ፍርድ ቤቶች አንድ የክልል ፍርድ ቤት ጉባዔ ይኖራቸዋል፤

2. የጉባዔው አባላት የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች እንዲሁም

www.chilot.me



የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ናቸው፤

3. በጉባዔው ላይ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የክልሉ ፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ኃላፊና የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው ተሳታፊ ይሆናሉ፤

4. ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው የጉባዔው አባላት ያልሆኑ ዳኞችና አግባብ ያላቸው የክልሉ መንግሥት የቢሮ ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦች በጉባዔው እንዲሣተፉ ሊጋበዙ ይችላሉ፤

42. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. በዳኝነት ሥራ አስተዳደር ረገድ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሄ የመስጠት፣

2. የዳኝነት አሠራር የሚሻሻልበትን መንገድ ፈልጎ ለፍርድ ቤቶች መመሪያ የመስጠት፣

3. አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም የነበሩት እንዲሻሻሉ ለክልሉ ምክር ቤት ሃሣብ የማቅረብ፣ እና

4. ለጉባዔው ሥራ አፈፃፀም ተገቢውን ደንብ የማውጣት

43. የጉባዔው አሠራር

1. የጉባዔው ሰብሳቢ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ይሆናል፤

2. ጉባዔው ፀሐፊውን ይመርጣል፤

3. ጉባዔው በአመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሆኖም ከጉባዔው አባላት አንድ ሦስተኛው እጅ ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠየቅ ሰብሳቢው ስብሰባውን ይጠራል፤

4. ከጉባዔው አባላት ሁለት ሦስተኛው እጅ ከተገኘ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

5. የጉባዔው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይሰጣል። ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል።

ምዕራፍ አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

44. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ጉዳዮች በክልሉ ሥልጣን ሥር የሚሸፍኑ እስከሆኑ ድረስ ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

45. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 5 ቀን 1988

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት